No 2112/2013
Date 11.9.2013

*"አጽናኑ ሕዝቤን አጽናኑ።" (ኢሳ. 40፥1)*

## ከሕጋዊው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ የተሰጠ መግለጫ።

በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ የሚመራውና በስደት ላይ የሚገኘው ሕጋዊው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ 38ኛውን መደበኛ ስብሰባ ከጥቅምት 27-30/ 2006 ዓ/ም (November 6-8, 2013) በኮሎምበስ ኦሐዮ ደብረ መድኃኒት መድኃኔዓለም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አካሂዷል። ቅዱስ ሲኖዶስም ስለ ስብከተ ወንጌል መስፋፋት፣ ቀኖና ቤተ ክርስቲያን መጠበቅ፤ ስለ ኢትዮጵያውያን ነጻነትና ክብር እንዲሁም ተያያዥ መንፈሳዊና ማኅበራዊ ጉዳዮች ላይ በሰፊው ተወያይቷል። በምልዓተ ጉባኤው ላይ ሲኖዶሱ ስለገዛው አዲስ የመንበረ ፓትርያርክ ጽ/ቤት ሕንጻ ጠቅላላ አስተዳደርና አጠቃቀም ሁኔታ በተመለከተ በሰፊው ተነጋግሯል። የመንበረ ፓትርያርኩ መግዛትና አገልግሎት መስጠት መጀመር የሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ የዕድገት መገለጫና ለቀጣዩ ትውልድም ቀዋሚ የታሪክ አሻራ መሆኑን አረጋግጧል። በመቀጠልም ጉባኤው ስለ ሕገ ቤተ ክርስቲያን መከበር፣ ስለ ሐዋርያዊ ተልእኮ መስፋፋትና ወደፊት በቅዱስ ሲኖዶሱ ሥር የሚቋቋሙ አዳዲስ አብያተ ክርስቲያናት ሕገ ቤተ ክርስቲያንን በሚገባ ተከትለው ስለሚተከሉበት ሁኔታ በሰፊው ተነጋግሯል፤ ጠቃሚ ውሳኔዎችንም አሳልፏል።

በመሠረቱ ቤተ ክርስቲያን በክርስቶስ የተገኘውን ፍጹም ነጻነት የምትመሰክር በመሆኗ ሰውን ሁሉ ከሰይጣንም ሆነ ከማናቸውም ክፉ ሥራ ነጻ እንዲወጣ ታስተምራለች። በመሆኑም ስለ ሰው ልጆች ነጻነትና ክብር እንዲሁም ሰብዓዊ መብት ዘወትር ማሰብ፣ ማስተማር፣ መጻፍና ጥብቅና መቆም ሐዋርያዊ ግዴታዋ ነው። እንደሚታወቀው ነጻነት የተፈጥሮ ጸጋ፣ ለሰው ሁሉ የተሰጠ መለኮታዊ ስጦታ ነው። አንድ ሕዝብ ነጻነት ከሌለው ህልውናው አደጋ ውስጥ ገብቷል ማለት ይቻላል። ምክንያቱም በክርስቶስ የተገኘው ፍጹም ነጻነት ለሰው ልጆች ሥጋዊና መንፈሳዊ ሕይወት መሠረት ነውና። ይሁን እንጂ በአገራችን የሕዝብንና የቤተ ክርስቲያንን አንድነት አጥፍቶ፣ ክብርና ነጻነት ነጥቆ የኢትዮጵያውያንና የኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ክብርና ነጻነት በእጅጉ የሚጋፋው በሥልጣን ላይ ያለው መንግሥት መሆኑ አሳዛኝ ነው። ከዚህም የተነሣ አገራችን ሁሉም ዜጎች በአንድነት፣ በነጻነትና በክብር የሚኖሩባት አልሆነችም። በመሆኑም ቅዱስ ሲኖዶስ በቤተ ክርስቲያናችንና በአገራችን ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ በሰፊው ከተወያየ በኋላ ከዚህ የሚከተለውን የአቋም መግለጫ አውጥቷል።



4127 Redwood Rd. Oakland CA 94619 Tel: (510) 530 3681

1ኛ/ በአገራችን ኢትዮጵያ በሥልጣን ላይ ያለው መንግሥት ፊደል ቀርጻ፣ ታሪክ ጽፋ፣ ትውልዱ ታሪካዊ ክብሩንና ማንነቱን እንዲያውቅ ያደረገች፣ ፈሪሃ እግዚአብሔርን በቃልና በኑሮ ያስተማረች፣ የሕዝብ ባለውለታ የሆነችውን፣ ጥንታዊት ሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን ገና ከመጀመሪያው ጀምሮ በጠላትነት ፈርጇት ይገኛል። በዚህም ምክንያት ጥንታውያን ገዳማቶቻችን ሲደፈሩና ሲመዘበሩ፤ መናንያን ከበዓታቸው ሲባረሩ፣ አብያተ ክርስቲያናት ሲቃጠሉ፣ ምእመናን ሲገደሉ በመገኛና ብዙኃን በሰፊው እየሰማን ነው። ለዚህም ተጠያቂው ቤተ ክርስቲያናችንን ለማዳከም ታጥቆ የተነሣው መንግሥት ነው። ከዚህም በተጨማሪ የመንግሥት ባለሥልጣናት ያለማቋረጥ በአደባባይ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን በማዳከም በመገናኛ ብዙኃን በማንአለብኝነት እየወቀሷትና እየከሰሷት ይገኛሉ። በመሠረቱ ይህ የግፍ ሥራ የተጀመረው ሕጋዊውን ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስን በማሳደድና የቤተ ክርስቲያኒቱን ሕጋዊ ክብር ገፎ ሲኖዶሱን በኃይል በማፍረስ ነው። እንደሚታወቀው ሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስም ስለ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ሕግ መጠበቅና መከበር ድምጹን ሲያሰማ ቆይቷል። በቅርቡ ደግሞ በኢትዮጵያ ያሉት አባቶችም በሥልጣን ላይ ያለው መንግሥት በቤተ ክርስቲያናችን ላይ የሚደርሰውን ግፍና በደል በድፍረት ገልጠው ሲናገሩ መስማታችን ቤተ ክርስቲያኒቱ ላይ እየደረሰ ያለውን ከፍተኛ ጫና በግልጽ ያሳያል። በየክፍለ ሀገሩ የሚገኙ የኢትዮጵያ ኦርቶዶስ ተዋሕዶ እምነት ተከታዮች በዜግነት መብታቸው ሐዋርያዊት የሆነችውን የኢትዮጵያ ኦርቶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ለማስፋፋት ቤተ ክርስቲያንን ለማነጽ አልቻሉም። ይህ አልበቃ ብሎ ያላቸውንም ይዞታ ይነጣቃሉ። ይህ ትውልድና ታሪክ የማይረሳው በደል የሚፈጽመው በመንግሥት ኃይላት ነው። ስለዚህ በቅድስት ቤተ ክርስቲያን ላይ የሚደርሰው ግፍና ሰቆቃ እንዲቆምና እንዲገታ በአጽንኦት እንጠይቃለን። ይህን እኩይ ተግባርም ሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ አጥብቆ ያወግዘዋል።

2ኛ/ ሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ በገለልተኛነት የሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት በሙሉ ለቤተ ክርስቲያናችን አንድነትና ዕድገት፣ እንዲሁም ለሐዋርያዊ ተልዕኮ መሳካት ከቅዱስ ሲኖዶስ ጋር አብረው እንዲሰሩ በድጋሚ ጥሪውን ያስተላልፋል።

3ኛ/ ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን በአገር ውስጥ በነጻነት መኖር ስላልቻሉና ኑሮውን ለማሸነፍና ራሳቸውን የሚረዱበት የሥራ እድል ባለማግኘታቸው ምክንያ ከሀገራቸው በመውጣት በመላው ዓለም በከፍተኛ ደረጃ በመሰደድ ላይ ይገኛሉ። በተለይም የኢትዮጵያ መንግሥት ከዓረብ አገሮች ጋር በመነጋገር የሥራ ኮንትራት አላቸሁ በማለት ገንዘብ እየተቀበለ የሚልካቸው ወጣት ኢትዮጵያውያት ልጆቻችን በብዙ ሽህ የሚቆጠሩ ናቸው። እነዚህ ወገኖቻችን ወደዓረብ አገሮች ከደረሱ በኋላ እየደረሰባቸው ያለው ግፍና ሰቆቃ በቃለት ሊገለጽ አይችልም። በአደባይ ይገደላሉ፣ አካላቸውም በየቦታው በአደባባይ ወድቆ ይታያል። በመሆኑም ከሚደርስባቸው ሥቃይ ለማምለጥ ካሉበት ሀገር ወደሌላ ሦስተኛ አገር ሲሰደዱም በባሕር ውስጥ ሰጥመው የሚቀሩት ወገኖቻችን ብዙዎች ናቸው። ይህም ለኢትዮጵጵያውያን ብቻ ሳይሆ ሰው ለሆነ ሁሉ አሳፋሪና እጅግ አሳዛኝ የሆነ ኢሰብአዊ ተግባር ነው። ቅዱስ ሲኖዶስም በኢትዮጵያውያን ላይ ስለደረሰው እንግልትና ሞት የተሰማውን ጥልቅ ኃዘን ይገልጻል።

4ኛ/ በአገራችን ኢትዮጵያ ሰው በሰውነቱ ስለማይከበር በነጻነት የማሰብ፣ የመናገርና የመጻፍ መብት የለውም። በዚህ ምክንያት ኅብረተሰቡን ወክለው፣ ስለ አገር ዕድገት፣ የዜጎች መብትና ነጻነት የሚሠሩ ተቀዋሚ ፓርቲ አባላት በየጊዜው ለእስርና እንግልት ይዳረጋሉ፤ ኢሰብአዊ የሆነ ነውርና ጥቃት ይፈጸምባቸዋል። የዚህ ችግር ሰለባ ከሆኑት መካከል በአገራችን

ያሉ ጋዜጠኞች፣ ስለ አገራቸው ነጻነት የሚታገሉ የፖለቲካ ፓርቲ አባላት ይገኙባቸዋል፤ ይህ ዓይነቱ ኢፍትሐዊ ድርጊት እንዲቆምና አገራችን የነጻነትና ሰብአዊ መብት የሚከበርባት ሰላማዊ አገር እንድትሆን ጥሪያችንን እናስተላልፋለን።

5ኛ) በመላው ዓለም የሚገኙ ኢትዮጵያውን ሁሉ በዘር፣ በሃይማኖትና በቋንቋ ሳይለያዩ እንደ ጥንቱ ዛሬም በፍቅርና በሰላም እንዲኖሩ፣ ከፋፋዩን የመንግሥት ፖሊሲ በመቃወም ለአንድነታቸውና ለፍቅራቸው ዘብ እንዲቆሙ ቅዱስ ሲኖዶስ እያሳሰበ ለዘመናት ተከብሮና ተጠብቆ በቆየው አንድነትና ፍቅር ጸንተው በመተሳሰብና በመከባበር አብረው እንዲኖሩ ቅዱስ ሲኖዶስ አደራ ይላል።

6ኛ/ በመጨረሻም 38ኛውን የቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ በማስተናገድ የደከሙትንና የተባበሩትን በኮሎምበስ፤ ኦሀዮ ደብረ መድኃኒት መድኃኔዓለም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ካህናትን፣ የአስተዳደር ቦርድ አባላትንና መላውን ሕዝበ ክርስቲያን በማመስገንና አባታዊ ቡራኬ በማስተላለፍ ጉባኤው በሰላም ተጠናቋል።